# የልጅነት፡ ክብር - የተስፋው፡ ቃል፡ ወራሽነት

አብርሃም፡ የእግዚአብሔር፡ ዘላለማዊ፡ ሃሳብ፡ የተንፀባረቀበት፡ የእምነት፡ አባት፡ ነው። አብርሃም፡ ካለህበት፡ አገርና፡ ከዘመዶችህ፡ ተለይተህ፡ እኔ፡ ወደ፡ ማሳይህ፡ ስፍራ፡ ውጣ፡ የሚል፡ የእግዚአብሔር፡ ቃል፡ በመጣለት፡ ጊዜ፡ እግዚአብሔርን፡ ታዞ፡ ወጣ። ከዚህ፡ ትእዛዝ፡ ጋር፡ የእግዚአብሔር፡ የተስፋ፡ ቃል፡ ወደ፡ አብርሃም፡ ደረሰ። አንድ፡ ልጅ፡ እንኳ፡ ያልነበረውን፡ አብርሃም፡ እግዚአብሔር (1) እጅግ፡ አበዛኋለው፤ (2) ለብዙ፡ አህዛብም፡ አባት፡ ትሆናለህ፤ (3) ሕዝብ፡ አደርግሃለው፤ (4) ነገስታት፡ ካንተ፡ ይወጣሉ፤ (5) ለአንተና፡ ለዘርህ፡ አምላክ፡ እሆንሃለው፡ የሚልን፡ አስደናቂ፡ የተስፋ፡ ቃል፡ ሰጠው (ዘፍ 17)። የተስፋው፡ ቃል፡ በመጣለት፡ ጊዜ፡ አብርሃም፡ የራሱን፡ ሁኔታ፡ ተመልክቶ፡ ባለማመን፡ ምክንያት፡ አልተጠራጠረም። ነገር፡ ግን፡ የእግዚአብሔርን፡ ኋይልና፡ ሁሉን፡ ቻይነት፡ ተመልክቶ፡ እግዚአብሔርን፡ አመነ። እምነቱም፡ በእግዚአብሔር፡ ፊት፡ ፅድቅ፡ ሆኖ፡ ተቆጠረለት (ሮሜ 4)። እንግዲህ፡ እግዚአብሔር፡ በእምነት፡ የመጽደቅን፡ መርህን፡ ሕግ፡ ከመምጣቱ፡ በፊት፡ በአብርሃም፡ በኩል፡ እንዳደረገ፡ እንመለከታለን። የአብርሃም፡ የተስፋ፡ ቃል፡ ዋና፡ ነገር፡ በሰውና፡ በእግዚአብሔር፡ መካከል፡ በእምነት፡ ላይ፡ የተመሰረተ፡ ግንኙነት፡ መቆሙ፡ ነው።

እግዚአብሔር፡ ለአብርሃም፡ የሰጠው፡ የተስፋ፡ ቃል፡ ለአብርሃምና፡ ለዘሩ፡ የተሰጠ፡ የተስፋ፡ ቃል፡ ነው። የእግዚአብሔር፡ ቃል፡ ለብዙ፡ እንደሚናገር፡ ለአብርሃምና፡ ለዘሮቹ፡ አይልም። ነገር፡ ግን፡ ለአንድ፡ እንደሚናገር፡ ለአብርሃምና፡ ለዘሩ፡ ይላል። እንግዲህ፡ የአብርሃም፡ ዘር፡ ማነው? ዘሩ፡ ክርስቶስ፡ ነው። (ገላቲያ 3፡16)። ክርስቶስ፡ በነገር፡ ሁሉ፡ ወንድሞቹን (እኛን) ሊመስል፡ ስለተገባው፡ የአብርሃምን፡ ዘር፡ ይዚል (ዕብራውያን 2፡ 15-16)። እንግዲህ፡ በክርስቶስ፡ ከሆንን፡ የአብርሃም፡ ዘር፡ ነን። የአብርሃም፡ ዘር፡ ከሆንን፡ ደግሞ፡ የተስፋው፡ ቃል፡ ወራሾች፡ ነን (ገላቲያ 3፡29)። ወገኖቼ፡ ሆይ፡ በክርስቶስ፡ ኢየሱስ፡ የአብርሃም፡ በረከት፡ ወደኛ፡ መጥቷል። ስለዚህ፡ ጉዳይ፡ ቃሉ፡ ሲናገር፡ "በእንጨት፡ የሚሰቀል፡ ሁሉ፡ የተረገመ፡ ነው፡ ተብሎ፡ ተጽፎአልና፡ ክርስቶስ፡ ስለ፡ እኛ፡ እርግማን፡ ሆኖ፡ ከሕግ፡ እርግማን፡ዋጀን፤ የመንፈስን፡ ተስፋ፡ በእምነት፡ እንድንቀበል፥ የአብርሃም፡ በረከት፡ ወደ፡ አሕዛብ፡ በኢየሱስ፡ ክርስቶስ፡ ይደርስላቸው፡ ዘንድ" ይለናል (ገላ 3፡ 12-13)።

ቤተ፡ ክርስቲያን፡ የአብርሃም፡ ዘር፡ ነች። እያንዳንዳችን፡ የክርስቶስ፡ ሆነን፡ የአብርሃም፡ ዘር፡ ሆነናል። ለአብርሃም፡ የተባለው፡ በረከት፡ ለቤተ፡ ክርስቲያን፡ ደርሷል። ስለዚህ፡ ዛሬ፡ ቤተ፡ ክርስቲያንን፡ የገሃነብ፡ ደጆች፡ አይቋቋምአዋትም። ይልቁንም፡ የጠላቷን፡ የዳቢሎስን፡ ደጆች፡ በኋይል፡ ትወርሳለች። ይህም፡ በክፋው፡ የተያዙትን፡ በክርስቶስ፡ ወንጌል፡ ነጻ፡ በማውጣትና፡ ወደ፡ እግዚአብሔር፡ መንግስት፡ በማፍለስ፡ ነው። ህዝብና፡ ነገስታት፡ ከአብርሃም፡ ወገብ፡ ይወጣሉ፡ እንደተባለ፡ እግዚአብሔር፡ በክርስቶስ፡ የአብርሃም፡ ዘር፡ የሆንነውን፡ የካህናት፡ መንግስት፡ አድርጎናል። ከርሱም፡ ጋር፡ ለዘላለም፡ እንነግሳለን። ሕግም፡ ደግሞ፡ ከጽዮን፡ (ከቤተ፡ ክርስቲያን) ይወጣል። የእግዚአብሔርም፡ ቤት፡ ተራራ፡ ከተራሮች፡ ሁሉ፡ በላይ፡ ከፍ፡ ይላል። ያም፡ ማለት፡ ቤተ፡ ክርስቲያን፡ በአለም፡ የሞራል፡ የበላይነትና፡ የገዢነት፡ ስፍራ፡ ይዛ፡ ከፍ፡ ብላ፡ ትታያለች፡ ማለት፡ ነው። ወገኖቼ፡ በክርስቶስ፡ የአብርሃም፡ ዘር፡ ሆነን፡ ከግንዱ፡ ጋር፡ ስለተጣበቅን፡ የእግዚአብሔር፡ ልጆች፡ ሆነን፡ የተስፋው፡ ቃል፡ ወራሾች፡ ሆነናል።